# “ሃምሳ ቢወለድ፣ ሃምሳ ነው ጉዱ ...”

ደነቀው ተግባሩ ከለንደን

“ሃምሳ ቢወለድ፣ ሃምሳ ነው ጉዱ፣
ያበበ ዓይነቱ፣ የተባረከው፣ ይበቃል አንዱ።"

ልብ ላለው ጎበዝ፣ አቤን ለመሰለ፣
ነፍጥ አያስፈልግም፣ የተቀባበለ፣
ትንፋሹም ያቆስላል፣ ከተቀጣጠለ።
የአበበ ድምፁ፣ ሲጮኽ እንደ መብረቅ፣
ያንን ዘባራቂ፣ ውሸት ሲዘባርቅ፣
ሲይደርገው አይተናል፣ ልብልብ የቁም ደረቅ።
ጫካ አያስፈልግም፣ "ጥራኝ ደኑ!” አትበሉ፣
ከተማም ጫካ ነው፣ ስብሰባም ደን ነው፣ ወኔ ላለው ሁሉ።

አበበ ገላውን፣ የቴዎድሮስን ቁራጭ፣
ለይቼ አላየውም፣ ከሞገስ አስገዶም፣ ከአብርሃም ደቦጭ።
በሮም አደባባይ፣ እንደ ዘርዓይ ደረስ፣
ዲሲም ተደገመ፣ የጀግና ልጅ መንፈስ።
እናት ኢትዮጵያ፣ ሌላም ልጅ ይውጣልሽ፣
የሚሚ ሥብሃቱን፣ አፍ የሚዘጋልሽ።

ከባዱ በረዶ፣ ዲሲ የወረደው፣
የመለስን አንገት፣ ቅጠል አደረገው።
ከመንጋው መካከል፣ አንበሳው ሲያገሳ፣
አምባገነን ሁሉ፣ በያለበት ከሳ።

መለሰ ዜናዊ፣ ያለበት ጠፍቶበት፣
አንገቱ ተጣሞ፣ እንደ ተኛች ድመት፣
አፉም ተሽብሽቦ፣ እንደ ስንቅ ከረጢት።
ዓይኑን ገለጥ አርጎ፣ መልሶ ለመክደን፣
ተጨንቆ ነበረ፣ በንደት ሰመመን።
ሰማዩ፣ መሬቱ፣ በጣም ዞሮበታል፣
የውርደቱን ሸክም፣ መቻል አቅቶታል።
ታዲያ መለስም፣ ሰው እንደ መሆኑ፣
አቤት ማናደዱ! አቤት ማሳዘኑ!
ለካስ ቅጠል ኖሯል፣ መለሰ ዝሆኑ?!

ያ ለምለሙ ችግኝ፣ በጣም የተዋበ፣
የትግልን ምግብ፣ እየተመገበ፣
በኦባማ ግቢ፣ ዲሲ ውስጥ አበበ።
አበበ መብረቁ፣ አዳፍኔው ይሉሃል፣
እኔ ልሙትልህ፣ ምስጋና ያንስሃል፣
እግዜር ይጠብቅህ፣ ብልህ ይበቃሃል።

የመለስ ዘበኛ፣ ስንት አስተዛዘበን!
ምን ዓይነት ቀልድ ነው? ይህ ዓይነት ማላዘን?!
ከሞቱ በኋላ፣ "እንገልሃለን?!”

ወገኖች ከታሪክ፣ ታሪክን ተማሩ፣
ምክንያት አታብዙ፣ ለሰልፍ ስትጠሩ፣
ከአበበ ገላው፣ ምሳሌን አስቀሩ።